## እ.ኤ.አ ከኦገሰት 21-31/2019 የነበረው

## የአየር ሁኔታ ግምገማ


ባለፉት የኦገስት ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ዕርጥበታማዉ የአየር ሁኔታ በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክሮ የተስተዋለ ሲሆን፤ በተለይም በመካከለኛዉ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ ተጠናክሮ ነበረ የሰነበተዉ፡፡ በዚሁ መሰረት በብዙ ቦታዎች ላይ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት እንደነበረ የተሰበሰቡ የዝናብ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት፣ በአንዳንድ የትግራይ፣ የአማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የመካከለኛዉ እና ምዕራብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የጋምቤላ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እስከ 94 ሚሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ ደጋማ ሰፍራዎች፣ በአፋር፣ በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሀረሪ፣ ድሬዳዋ እና ሰሜን ሱማሌን ጨምሮ በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ 46.5፣ በአቦምሳ 30.4፣ በአዲግራት 32.4 እና 35.8፣ በአይራ 53.4፣ በሀረማያ 42.6፣ በአሶሳ 37.2፣ በሀዋሳ 35.8፣ በአምባ ማሪያም 40.4፣ በቻግኒ 32.6 እና 32.0፣ በኮምቦልቻ 36.6፣ በጨርጨር 35.7፣ በደብረማርቆስ 32፣ በደብረታቦር 32.5፣ በዳንግላ 35.7፣ በደባርቅ 41.1፣ በደምቢዶሎ 35.2፣ በደብረወርቅ 33.8 እና 37.8፣ በእነዋሪ 51.5 እና 35.6፣ በፍቼ 97.0 እና 46.7፣ በጋምቤላ 56.8 እና 30.5፣ በጊምቢ 37.3፣ 32.6 እና 31.9፣ በጊኒር 34.0፣ በጎሬ 30.3 እና 49.0፣ በሆሳና 52.5 እና 42.8፣ በጅማ 33.3፣ በካቺስ 32.7፣ በመሃል ሜዳ 30.2፣ በማንኩሽ 37.0 እና 81.0፣ በማሻ 72.7፣ 50.0 እና 30.6፣ በሞጣ 30.7፣ በመካነሰላም 34.5 እና 46.8፣ በሚሌ 38.6፣ በማይፀም 32.2፣ 68.8፣ 94.0 እና 36.9፣ በአዳማ 47.0፣ በነቀምቴ 34.7፣ በሻምቡ 37.5፣ በሲሪንቃ 37.2፣ በወላይታ ሶዶ 31.6 እና 34.0፣ በዬትኖራ 52.2፣ በጭፍራ 35.2፣ በጊዳ አያና 50.0 እና 48.0፣ በጉንዶ መስቀል 33.0፣ 40.6 እና 32.8፣ በፉኝዶ 65.4፣ በሳምሪ 44.5፣ በእንጅባራ 44.5፣ በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም  በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች በሚገኙ


በሁሉም ዞኖች ላይ፣ ከአፋር ክልል በዞን 03 እና 05፣ ከኦሮሚያ ክልል በቄለም፣ በሆሮ ጉዱሩ፣ በምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ፣ የኢሉአባቦራ እና ጅማ፣ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ እንዲሁም በሁሉም የሸዋ ዞኖች ላይ በአርሲና ባሌ ደጋማ ስፍራዎች ላይ፣ ከደቡብ ክልል በሸካ እና ከፋ፣ በቤንችማጂ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከምባታ፣ በዳዉሮ፣ የሀላባ ልዩ ወረዳ፣ የኮንታ ልዩ ዞን፣ በወላይታ እና በሲዳማ፣ ከሱማሌ ክልል በፋፉን ዞን ላይ ከ25-317 ሚ.ሜ የሚደርስ ለ5-11 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት የአፋር ክልል ዞኖች ላይ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጋሞጎፋ፣ በሰገን ህዝቦችና በጌዴኦ፣ በጉጂና ባሌ ቆላማ ስፍራዎች ላይ 5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በትግራይ፣ በአማራ እና ጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ፣ ከጥቂት የዞን 01 በስተቀር በሁሉም የአፋር ክልል ዞኖች፣ ከጥቂት የሚዕራብ ወለጋ ዞን በስተቀር በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በአርሲ እና ባሌ፣ አንዳንድ የጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ በአንዳንደድ የምስራቅና ምዕራብ ሐርጌ፣ በፋፈንና ሲቲ ዞኖች፣ በጥቂት የአሶሳ፣ መተከል እና ከማሽ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ ስርጭት ነበራቸዉ (ካርታ 3) ።


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





በወቅቱ ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት የኦገስት ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ የሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ የመኸር ሰብል አብቃይና የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በመካከለኛዉ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ የተጠናከረ የእርጥበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ የእድገት ደረጃ እና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለጓሮ አትክልት፣ ለዕፅዋት ልምላሜ፣ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት የጎላ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ የትግራይ፣ የአማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የመካከለኛዉ እና የምዕራብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የጋምቤላ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በከባድ ዝናብ ምክንያት ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች፣ በአፈር ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ መጠነኛ ጉዳት ነበረው፡፡ በአንጻሩ ባለፉት አሰራ አንድ ቀናት የተገኘው እርጥበት ቀደም ባሉት ቀናት እርጥበት ባልተዳረሰባቸው እና እጥረት ለነበረባቸው ቆላማ አካባቢዎች ለሚኖሩት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከኦገስት 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ በአብዛኛው የአባይ፣ የተከዜ፣ የባሮአኮቦ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የኦሞ ጊቤ፣ የአዋሽ፣ የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ያገኙ ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ፣ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛውና መካከለኛው አፋር ደናክል እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ኪስ ቦታዎች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ላይ እንደነበራቸው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ በቂ የሆነ የውሃ መጠን አግኝተዋል፡፡ ይህም ለተለያዩ የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ አዎንታዊ የሆነ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ከላይ ከተጠቀሱት ተፋሰሶች ውጭ ያሉ ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2019 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተዳከሙ የሚሄዱበት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየቀነሰ ይሄዳል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋ፣ የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋና የሲዳማ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ የደቡብ ኦሞ፣ የሰገን ህዝቦች፣ የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ የአፋር ዞን 3፣ 4 እና 5 እንዲሁም የፊቅ፣ የደጋሃቡር፣ የጅጅጋና የሽንሌ ዞኖች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ. ኤ. አ ከሴፕቴምበር 1-10 /2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር አብቃይና የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት ሁኔታው አሁን ባለው ሁኔታ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም አልፎ

በአንዳንድ አካባቢዎች ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ያለዉ እርጥበት የሚኖራቸው ሲሆን፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለይም መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ከላይ በትንበያ በተጠቀሱት ዞኖች እያከናወኑ ላሉት የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ የሚጠበቀው የተጠናከረ እርጥበት ገንቢ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተለይም ዘግይተዉ ለተዘሩ፣ በተለያየ እድገት ደረጃ እና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችና ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር የሚጠበቀው እርጥበት ጉልህ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ከማሻሻሉም በተጨማሪ የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪ ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ በአንዳንድ ቦታዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ከመፍጠሩ ጋር ተያይዞ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸውና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በውኃ መብዛት በሚጠቁ ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና እንዲሁም በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ሰለሚችል የሚመለከተው ክፍል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ አረምን በወቅቱ በማረም ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10 /2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረው  የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህም መሰረት በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ እና የላይኛው

ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛዉና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ አፋር ደናክል፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተቀሩት የተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚሆን ይጠበቃል። ሆኖም ግን በተለይ የዝናብ ስርጭታቸው ከመደበኛ በላይ የሚጠበቅባቸው አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ከመዝነቡ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተት እና የወንዞች ሙላት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።